# ሰብዓዊ መብት ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት

- በበበቀረቡ አቤቱታዎች ላይ ምላሽ ይሰጣል፤ ምላሽ እንዲሰጥ ያደርጋል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤
- ለስራ ክፍሉ በረጂ ድርጅቶች የሚሰጡ የገንዘብ፣ የቁሳቁስና ሌሎች ድጋፎች አግባብ ባለው ሁኔታ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ያስተባብራል፤
- በሰብዓዊ መብት ጉዳዮች ዙሪያ ከሚሰሩ ክልላዊ፣ ሀገር በቀል፣ አህጉራዊና አለም አቀፋዊ ተቋማት ጋር በቅንጅት የሚሰሩ ተግባራትን ያስተባብራል፤
- በቢሮው ተፈጻሚ የሚሆኑና ዳይሬክቶሬቱን የሚመለከቱ ዝርዝር የአሰራር መመሪያዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፤
- የሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶች እና ባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን አስመልክቶ በወጡ፣ አዲስ በሚወጡ ህጎች እና አሠራሮች ዙሪያ የሚታዩ ክፍተቶችን በተመለከተ ከህግ ምክር፣ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት ወይም ከፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና የህግ ምርምር ኢንስቲቲዩት ጋር በመሆን የዳሰሳ ጥናት እንዲጠና ያደርጋል፤
- ከመደበኛ ወንጀልና ሙስና ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬቶች፣ ከፍትሐብሔር ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት፣ ከሰነዶች፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ ማህበራትና ጠበቆች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት እና ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የሴቶች፣ ህጻናትና የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን የሚመለከቱ የዉይይት እና የተሞክሮ ልዉዉጥ መድረክ ያዘጋጃል፣